# በኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ የኩባንያዎች መመዝገብ

## መግቢያ

**የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ በኢትዮጵያ የፋይናንስ ሥርዓት ውስጥ አዲስ የልብ ምት ነው።**

ላለፉት በርካታ ዓመታት የሃገር ውስጥ ኩባንያዎች በባንክ ብድር ጥገኛ በመሆን እና በግል ካፒታል ላይ በመደገፍ እድገት ለማስመዝገብ ሲሞክሩ ታይቷል። ነገር ግን አሁን ባለው አሰራር አዲስ የፋይናንስ በር ተከፍቷል። የካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 መውጣቱ እና የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ መቋቋሙ ኩባንያዎች ለሕዝብ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን በማውጣት እና በመሸጥ ገንዘብ ሊሰበስቡ የሚችሉበትን መንገድፈጥሯል። ምዝገባ ከግብይት በላይ ፋይዳ ያለው ሆኖ ኩባንያዎች ከግል ድርጅት ወደ ህዝባዊ ተቋምነት የሚሸጋገሩበት ታሪክ ነው። ከጡረታ ፈንድ፣ ከውጪ ኢንቨስተሮች እና ከኢትዮጵያውያን ትልቅ ካፒታል ለመሰብሰብ የሚደረግ ጉዞ ነው።

## የሕግ የበላይነት እና የጨዋታው ደንቦች

እያንዳንዱ ታላቅ ጉዞ ጠንካራ መሠረት ያስፈልገዋል። ለማንኛውም ትልቅ ኩባንያ ወደ ገበያው የሚወስደው መንገድ፣ ያ መሠረት በሁለት ሰነዶች ላይ የተገነባ ነው። የመጀመሪያው የካፒታል ገበያ አዋጅ ሲሆን ይህንን እንደ የኢትዮጵያ አዲስ የካፒታል ገበያ መሰረት ጣይ ህግአድርገው ያስቡት። ምክንያቱም ይህ አዋጅ የገበያውን ታማኝነት ገለልተኛ ጠባቂ የሆነውን የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣንንአቋቋመ። አዋጁ ለባለሥልጣኑ ሁሉንም የካፒታል ገበያ ጉዳዮች የመቆጣጠር ሥልጣን ይሰጠዋል፣ በተለይም ትልልቅ ኩባንያዎች አክሲዮኖቻቸውንበሃገሪቱ ወይም ከሃገር ውጪ ለሚገኙ ለማናቸውም ኢንቨስተሮች የሚሸጥበትወሳኝ "የሕዝብ አቅርቦት" ሽያጭ ሂደት የመቆጣጠር ስልጣን ተሰጥቶታል።

ሁለተኛው ሰነድ የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ መተዳደሪያ ደንብ ነው። አዋጁን ለግብይት ስርዓቱ እንድ መሰረታዊ ህግ ከቆጠርን፣የገበያው መተዳደርያ ደንብ የገበያው የራሱ እና የአባላቱ ዝርዝር የማስተዳደርያ ሰነድ ነው። ገበያው ፈቃድ ያለው ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት እንደመሆኑ መተዳደርያ ደንቡን ለተመዘገበ ኩባንያ በገበያው ተመዝግቦ በሚገኝበት ጊዜ ሁሉ ሊያሟላው ስለሚገባ ትክክለኛ የምዝገባ መስፈርቶች፣ፎርሞች እና መመዘኛዎች ደንግጎ ይገኛል። ስለዚህ ማንኛውም በገበያው ሊመዘገብ የሚፈልግ ኩባንያ ስኬታማ ለመሆን የባለስልጣኑን የምዝገባ መስፈርቶች እና የገበያውን መተዳደርያ ደንቦችን ማሟላት አለባቸው። አንዱ ካለሌላው ሊኖር የማይችል እርስ በርስ የተሳሰሩ እና የተደጋገፉ መስፈርቶች ናቸው።

# በኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ የኩባንያዎች መመዝገብ

## ሁለት ደረጃ ገበያዎች

የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ለሁሉምየሚስማማ አንድ አይነት መጠን ያለው የግብይት መድረክ አይደለም፤ ለተለያዩ ኩባንያዎች የተለያዩ መስፈርቶች እና ወደ ግብይት መግቢያ በሮች አሉት። የመጀመሪያው ለግዙፍ ኩባንያዎች ምዝገባ እና ግብይት የተነደፈው የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ዋናው የገበያ ቦርድ ነው። የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ዋናው የገበያ ቦርድ በሚገባ ለተደራጁ ባንኮች፣ በመንግስት ለተያዙ እድሜ ጠገብ ድርጅቶች፣ ለዓመታት የተረጋገጠ ትርፍ ላላቸው ኮርፖሬሽኖች የተነደፈ ነው ማለት ይቻላል።

የዚህ የዋናው የገበያ ቦርድ የምዝገባ እና የግብይት መስፈርቶች ጥብቅ ሲሆኑ ከእነዚህም መስፈርቶች ውስጥ ኩባንያው ያለፉት የሶስት ዓመት ፋይናንሻል ስቴትመንት ማቅረብ የሚችል፣ ከሶስቱ አመት ውስጥ ቢያንስ በአንዱ አመት የትርፍ ሪከርድ ያለው መሆኑን የሚያሳይ ሰነድ በኦዲት ሪፖርት መልክ ማቅረብ የሚችል፣ ቢያንስ ግማሽ ቢሊዮን ብር የገበያ ካፒታላይዜሽን ወይም በባለአክሲዮኖች የተያዙ አክሲዮኖች ያለው መሆኑን ሰነድ ማቅረብ የሚችል እና የምዝገባ ጥያቄ ከቀረበባቸው ቢያንስ አስራ አምስት በመቶ (15%) የአውጭው አክሲዮኖች ቢያንስ በ300 የህዝብ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለቤቶች ወይም እንደ የውክልና ሻጭ የሚያገለግሉ የኢንቨስትመንት ባንክ ወይም በተቋማዊ ኢንቨስተር የተያዘ መሆኑን ማስረጃ ማቅረብ የሚችል የሚሉ መመዘኛዎች ይገኙበታል።

በዚህ እንደ ልዩነት ሊነሳ የሚችለው በገበያው መተዳደሪያ ደንብ ከላይ የተጠቀሰው የአምስት መቶ ሚሊየኑ መስፈርት ያለ ቢሆንም ቢያንስ ሁለት ቢሊዮን ብር ካፒታላይዜሽን ያለው አውጪ አሥር በመቶ (10%) ብቻ ለግብይት የቀረበ አክሲዮን እንዲኖረው ሊፈቀድለት ይችላል።

ሌላኛው የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ የአዳጊ ገበያ ቦርድ ነው። ይህ የገበያ ቦርድ ለአዳጊ ኩባንያዎች፣ የማደግ አቅም እና ተስፋ ላላቸው አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የተነደፈ ነው።

በዚህ ቦርድ ለመመዝገብ የሚያበቁ መስፈርቶችን በተመለከተ አውጪው የሁለት አመት የስራ አፈጻጸም ማቅረብ የሚችል፣ ቢያንስ የሁለት አመት የሥራ አፈፃፀም መዝገብ ያለው እና ከፍተኛ ድርሻ ያለው ዋና ኢንቨስተርነትን ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣ አውጪው የሂሳብ መዝገብ የማይዝ ከሆነ እና የኦዲት ሪፖርት ማቅረብ ካልቻለ ዋና ኢንቨስተሩ ባለፉት ሁለት ዓመታት የሥራ ክንውኖች ገቢውን በትንሹ ሃያ በመቶ መጠን የማደግ ተስፋ ያሳየ መሆኑን ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል፣ የምዝገባ ጥያቄ ከቀረበባቸው ቢያንስ 10% የአውጭው አክሲዮኖች ቢያንስ በሃምሳ የህዝብ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለቤቶች ወይም እንደ የውክልና ሻጭ በሚያገለግሉ የኢንቨስትመንት ባንኮች ወይም በተቋማዊ ኢንቨስተሮች መያዝ ያለበት መሆኑን የሚስማማ፣ አውጪው ሲመዘገብ ቢያንስ ሃምሳ ሚሊዮን ብር የሚሆን ጠቅላላ የገበያ ካፒታላይዜሽን (ማለትም የተመዘገበ እና የተከፈለ ካፒታል) ያለው መሆኑን ማሳየት የሚችል የሚሉት የምዝገባ መስፈርቶች ይገኙበታል።

## የደንበኛ ሳቢ መግለጫ ዝግጅት እና ምዝገባ

ደንበኛ ሳቢ መግለጫ ለማያውቋቸው ሰዎች የተጻፈ የአንድ ኩባንያ የሕይወት ታሪክ ነው ማለት ይቻላል። በካፒታል ገበያ አዋጅ ደንበኛ ሳቢ መግለጫ ማለት በአክሲዮን ኩባንያ ወይም በኩባንያው ስም የወጣ እና ኩባንያው ስላወጣቸው አክሲዮኖች፣ የእዳ ሰነዶች፣ ወይም ሌሎች የኩባንያው ሰነድ ሙዓለ ንዋዮች ባህሪ፣ እና ዓላማ የሚገልጹ መረጃዎችን በማካተት ሕዝብ እንዲገዛ ጥሪ የሚደረግበት የጽሁፍ ሰነድ ወይም ሕትመት ነው። ዚህ መሰረት ደንበኛ ሳቢ መግለጫ በአውጪው ድርጅት በኩል በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ኢንቨስትመንት አማካሪ ወይም የኢንቨስትመንት በ ባንክ የሚዘጋጅ ሲሆን እንደሁኔታው የኦዲት ሪፖርት፣ ገለልተኛ የህግ አስተያየት እና ሃብት ግመታን ያካተተ መሆን አለበት። ይህ ሰነድ የአውጪውን ያለፉት ሶስት አመታት የኦዲት ሪፖርት፣ የገቢ አጠቃቀም፣ የኢንቨስትመንት ፖሊሲ፣ አውጪው ያለውን ስጋት፣ሰነዱ ላይ ስለተገለጹ ጉዳዮች ሃላፊነት የሚወስዱ የአውጪው ስራ አመራሮች፣ እና ሌሎች ዝርዝር ስለ አውጪው ቁመና ሙሉ መረጃ የያዘ ሰነድ ነው። አውጪው ይህን ሰነድ ለባለሥልጣኑ አቅርቦ ሳያስመዘግብ ሰነደ ሙዓለ ንዋዩን ለሕዝብ ማውጣት እና መሸጥ አይችልም።

አውጪዎች በዚህ ሂደት አልፈው በባለሥልጣኑ ተመዝግበው አዲስ ሰነዶችን በመጀመሪያ ደረጃ ገበያ ላይ አውጥተው ከሸጡ በኋላ ከላይ ያየናቸውን የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያን የምዝገባ መስፈርቶች ካለፉ በገበያው ተመዝግበው የሚገበያዩበት፣ መስፈርቶቹን ካላሟሉም እዛው ገበያ ላይ በልዩ ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ የግብይት ሥርዓት ሰነዶቹ የሚገበያዩበት አሰራር ተዘርግቷል።

# በኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ የኩባንያዎች መመዝገብ

## ከገበያው እና ባለሥልጣኑ የተሰጠ ማረጋገጫ

ከላይ እንደተገለጸው የተጠናቀቀው የደንበኛ ሳቢ መግለጫ መጀመሪያበባለሥልጣኑ መጽደቅ አለበት። የአውጪው ደንበኛ ሳቢ መግለጫ እንደደረሳቸው የባለሥልጣኑ ባለሙያዎች እያንዳንዱን መስመር ይመረምራሉ፣ ታሪኩ አሳማኝ ብቻ ሳይሆን የተሟላ እና እውነት መሆኑን ያረጋግጣሉ። ጥያቄዎች ወደ አውጪው እና ከአውጪው ማብራርያ መልስ ይሰጥባቸዋል። የአውጪው ደንበኛ ሳቢ መግለጫ በባለሥልጣኑ መመዝገቡ አውጪው ሰነዶችን ለሕዝብ እንዲሸጥ ህጋዊ ፈቃድ እንደመስጠት ነው። አውጪዎች በኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ በኩል ሊመዘገቡ እና ሰነዳቸውን ሊገበያዩ የሚችሉት ከዚህ ምዝገባ በኋላ መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል።

አውጪው በገበያው ለመመዝገብ ሲያመልክት የገበያው የምዝገባ ቡድን ሰነዶችን በማደራጀት በገበያው መተዳደሪያ ደንብ መስረት ለምዝገባ የሚያበቁ የአውጪው የድርጅት አስተዳደር፣ መዋቅር፣የወደፊት የማደግ አቅም፣ የመስራቾቹ ቁርጠኝነት እና ሌሎች ከላይ ያየናቸው ዋነኛ የገበያው የምዝገባ መስፈርቶችን ማሟላቱን ይመረምራሉ። የገበያው ምዝገባ ቡድን የአውጪው ሰነድ መሟላቱን ከገመገሙ እና ካረጋገጠ በኋላ በአውጪው እና በገበያው መካከል አውጪው በገበያው በመመዝገብ ሰነዶቹ በገበያው እንዲገበያዩ በገበያው መተዳደሪያ ደንብ ሊገዛ እና አክብሮ ሊሰራ ስምምነት ይፈጽማሉ።

## በገበያው የመመዝገብ ውጤት

አውጪው በገበያው ከተመዘገበ በኋላ አክሲዮኖች ለመጀመሪያ ጊዜ በገበያው የግብይት ስክሪን መታየት እና መገበያየት ይጀምራሉ። በአዋጁ እና ደንቡ መሰረት በገበያው መመዝገብ በአውጪው ላይ ቀጣይነት ያላቸውን ግዴታዎች ያስከትላል። አውጪው በየሩብ አመቱ የፋይናንስ ሪፖርት እንዲሁም በአመት አንድ ጊዜ ኦዲት ሪፖርት ለገበያው እና ለባለሥልጣኑ የማቅረብ ግዴታ አለበት። በገበያው መመዝገብ አውጪው ላይ ከዚህ በፈጠነ አኳሃን መረጃዎችን ይፋ የማድረግ ግዴታም ያስከትላል። ለምሳሌ አውጪው የአክሲዮኖቹን ዋጋ ምክንያታዊ ባልሆነ ሁኔታ እንዲጨምር ወይም እንዲቀንስ ሊያደርግ የሚችል ማንኛውንም መረጃ በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ ለገበያው ማሳወቅ አለበት። ዝምታአማራጭ አይደለም፤ ግልጽነት የገበያው የጫወታ ዋንኛ ህግ ነው።

## አዲሱ የአስተዳደር ሥርዓት

በኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ከተመዘገበ በኋላ አውጪው የሚኖረው ሕይወት አሠራሩን፣ የአስተዳደር ዘይቤውን በብዙ መልኩ የሚለውጥ ነው።መስራቾችንእና ቤተሰብን ብቻ ያቀፈ የቦርድ አባልነት ዘመን ያበቃል።ቢያንስ 30% የሚሆነውንየቦርዱን አባላት የሚያዋቅሩ ገለልተኛ ዳይሬክተሮችን ከአውጪው ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌላቸውን ግለሰቦች መሾም አለበት። አብዛኛውን ጊዜ በገለልተኛ ዳይሬክተር የሚመራ የኦዲት ኮሚቴ ከፍተኛ ቁጥጥር የሚያደርግ በመሆኑ ለአውጪው ጤናማ አሰራር ወሳኝ ነው።

ሌላው የአውጪው የዋና ሥራ አስፈፃሚ እና የቦርድ ሊቀመንበር ሚናዎች መለያየት አለባቸው፣ ይህም የኃይል ሚዛንን ያስጠብቃል። እንዲሁም ከአውጪው ተዛማጅ ወገን ጋር የሚደረግ ማንኛውም ግብይት ለምሳሌ ከአውጪው ዳይሬክተሮች ሌላ ኩባንያ ጋር፣ ከአውጪው ዋና ባለአክሲዮን ድርጅት ጋር የሚደረጉ ግብይቶች እና የመሳሰሉት በሚገባ ይፋ መደረግ አለባቸው።ይህም የግል ጥቅምን ከማስጠበቅ ይልቅ የህዝብ እምነት ማስጠበቅ በመሆኑ በአውጪው አስተዳደር አሰራር ትልቅ ለውጥ ሊያመጣ የሚችል ነው።

# በኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ የኩባንያዎች መመዝገብ

## ከገበያው እና ባለሥልጣኑ የተሰጠ ማረጋገጫ

አንድ በገበያው የተመዘገበ አውጪ ለገበያው ማሳወቅ ያለበትን ወሳኝ የሆነን መረጃ ሳያሳውቅ ቢቀር ወይም የፋይናንስ አቅሙ ቢወድቅ ባለሥልጣኑ የቁጥጥር መሳሪያዎቹን በመጠቀም ቅጣት ሊጥል፣የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ ወይም የኩባንያውን አክሲዮኖች በገበያው እንዳይገበያዩ ሊያግድ ይችላል።

ገበያውም በራሱ በኩል የአውጪውን ያልተገባ ድርጊት ለሕዝብ ሊያሳውቅ እና የገንዘብ ቅጣቶችን ሊጥል ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ በጣም ከባድ በሆኑ ጉዳዮች ለምሳሌ የአውጪው ሥር የሰደደ ህግ አለማክበር፣ የንግዱ ውድቀት እና ሌሎች ለምዝገባ የሚያበቁ መስፈርቶች ተብለው ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ የአንዱ መጓደል ከገበያው ምዝገባ ስረዛን ሊያስከትል ይችላል። ይህ ለአውጪው የኮርፖሬት መልካም ስምን የሚያጎድፍ አደጋ ነው።

ከምዝገባ ጋር በተያያዘ ባለሥልጣኑ እና ገበያው በአውጪው ላይ የሚያስተላልፉት ውሳኔ አውጪው ቅር በመሰኘት እና በመቃወም ይግባኝ ለካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ለማቅረብ ጉዳዩ በይግባኝ እንዲታይ ማድረግ ይችላል። የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ውሳኔዎች የገበያውን ተዓማኒነት ብሎም የኢንቨስተሮችን መብት ያስጠብቃሉ።